# የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ጉዳይ ተገቢ መፍትሔ እስከሚያገኝ ድረስ ንቁ ክትትልና ያልተቋረጠ ትግል ያስፈልጋል!

ኢሮብ-ማብሎ

የካቲት 2004

ኢትዮጵያዊያን የአልጀርስ ስምምነትንና የሄግ ውሳኔን በሚገባ መረዳትና የኢትዮጵያና የኤርትራ የዳር ድንበር ጉዳይ ነቅቶ መከታተል ይገባቸዋል። የድንበሩ ግጭትና መፍትሔውን በሚመለከት በርካታ ኢትዮጵያዊያን፣ የሕግ ተመራማሪዎችና ሌሎች ምሁራን፣ በወቅቱ ሰፋፊ ሕጋዊና ታሪካዊ ጥናቶችን ማቅረባቸው ይታወሳል። የኢሮብ ተወላጆችም በግልና በቡድን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶችንና የህዝባቸውን ሰብአዊና ዜግነታዊ መብቶችን ለማስከበር ሲሉ ታሪካዊና ወቅታዊ መረጃዎችን በማጣቀስ ሁናቴው በኢትዮድያዊያንና በዓለም-አቀፍ ማህበረ-ሰብ በግልጽ እንዲታወቅ ይረዳ ዘንድ በስፋት ጽፈዋል፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወራሪው የሻዕቢያ ሠራዊት በህዝብ ላይ የፈጸመውን አስከፊ ግፎች በዓለምአቀፉ ማህበረ-ሰብ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል። ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ደግሞ የኢሮብ መብት ተሟጋች ማህበር (ኢ.መ.ተ.ማ) በሻዕቢያ ሠራዊት ተጠልፈው ተወስደው ጠያቂ መንግሥት በማጣት እስከዛሬ ድረስ መዳረሻቸው ያልታወቀ ከ100 በላይ ዜጎችና በአልጀርስ ስምምነት መሠረት የተወሰነውና የሄግ ብይን ተብሎ የሚታወቀው የኢህአዴግ መንግሥት ያለ-ቅድመሁኔታ በተቀበለው መሠረት ድንበሩን ለማካለል ከሻዕቢያ ጋር ለመነጋገር ተደጋጋሚ ጥሪ ስለሚያቀርብባቸው የኢሮብ ህዝብ የሚኖርባቸውና ሌሎች ሰፋፊ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶችን በተመለከተ የፍትሕ-ያለህ ማለትን አላቋረጠም፣ ፍትሓዊ እልባት እስኪገኝ ድረስም ትግሉን አያቋርጥም።

የድንበራችን ጉዳይ ተገቢ መፍትሄ ባላገኘበት፣ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር "አካላይ መስመሩ የሚያልፍባቸው ቦታዎች ላይ የሚገኙ ቤቶች ለሁለት እንዳይከፈሉ እንነጋገር ብለን ብንማጸንም ሻዕቢያ አሻፈረኝ አለን" እያሉን ባሉበት፤ በሄጉ ውሳኔ ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆነው የኢሮብ መሬት ለኤርትራ መሰጠቱ በታወቀበት፤ አንዳንድ ያገዘዙ ደጋፊ ብልጣብልጦች በሚነዙት ባዶ ፕሮፓጋንዳ የሚታለሉ የዋህ ዜጎች ለጊዜው የኢትዮጵያ ሠራዊት በአከባቢው ተቀምጦ መኖሩን እንደዋስትና በመውሰድ መሬታችን እንዳልተሰጠ፣ ዳር ድንበሩ ለወደፊቱ በሚያስተማምን ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚታያቸው ወገኖቻችን መኖራቸው፤ የድንበር ጉዳይን በተመለከተ በኢሮብ ማብሎ (www.irobmablo.org) ላይ በወጡ ጽሁፎች ዙርያ በተለያየ መንገድ ከሚደርሱን አስተያየቶች ለመረዳት ችለናል። በነዚህ ወገኖቻችን ከሚሰነዘሩ አስተያየቶች ውስጥ "ምኑ ነው እናንተን የሚያስጨንቃችሁ! የኢትዮጵያ ሠራዊት እኮ የኢሮብን ዳር ድንበር ለመጠበቅ እስከ ማካታ ድረስ ዘልቆ ገብቶ ሰፍሯል! ከእንግዲህ ሻዕቢያ እንደገና መሬታችንን ይደፍራል ማለት ዘበት ነው! በመሆኑም ስለ ዳር ድንበራችን የመጨነቅ አስፈላጊነት አይታየንም....ወዘተ" የሚሉ ማጽናኛዎች ይገኙበታል። ይህንን ዓይነት አመለካከትና እምነት የሚጋሩ ወገኖቻችን በርካቶች እንዳይሆኑም ስጋቱ አለን። የአንድ ሃገር ሰራዊት በተወሰነ ቦታ መቀመጥ ብቻው የዛን አከባቢ ሉዓላውነት ለዘላቅነት መከበሩን አያመላክትም። በመሆኑም፤ የኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ጉዳይ ተገቢ መፍትሔ እስካላገኘ፣ ንቁ ክትትልና ያልተቋረጠ ትግል ያስፈልጋል ብለን ደግመን ደጋግመን ከማስረዳት/ከማሳሰብ ወደ ኋላ አንልም ብቻ ሳይሆን፤ ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር አስፈላጊውን ትግል ለማድረግ እንገደዳለን።

የአንድ ሃገር ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር መከበር፣ እቦታው ላይ ሠራዊት በማስፈር ብቻ የሚወሰን ቢሆን ኖሮ ዛሬ የኢትዮድያ ሰራዊት በሰፈረባቸው የኢትዮጵያ መሬቶች ላይ ሻዕቢያም ለሁለት ዓመታት ያህል ሰራዊቱን አስፍሮባቸው እንደነበረ ሁላችን የምናውቀው ነው። በኢትዮድያ ሰራዊት ተሸንፎ እስኪባረር ድረስም የኤርትራ ሉዓላዊ መሬትን አስከብርያለሁ ብሎ ይዝናና እንደነበረ የምንገነዘበው ነው። ሆኖም "ዕድሜ ለአቶ መለስ"! አሸናፊን ተሸናፊ፣ ተሸናፊን ደግሞ አሸናፊ ያደረገውን የአልጀርስ ውል በመፈረም ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን ሄግ ወስደው ለሻዕቢያ አስረክበውት ተመልሰዋል። ብይኑንም ያለ ቅድመ-ሁኔታ መቀበላቸውን በይፋ አውጀዋል። ይህንን ሕገ-ወጥ ብይን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ተቀብለናል ብለው ለዓለም አቀፉ ማህበረ-ሰብ ካወጁ በኋላ ዛሬ በተወረሩብን መሬቶች ላይ ሠራዊት ማስፈር ትርጉም የሚሰጥ ጉዳይ አይደለም። አቶ መለስ ራሳቸው ያሰፈሩትን ሠራዊት ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ተቀብየዋለሁ ባሉት የሄግ ብይን መሠረት ከኤርትራ መንግሥት ጋር ተነጋግረን የድንበሩን ጉዳይ በጋራ ስምምነት ስለፈታነው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከያዘው ቦታ እንዲነሳ አዝዣለሁ ሊሉን እንደሚችሉ ልንገነዘብ ይገባል። የአቶ መለስ ጭንቀት ቤቶች ለሁለት መከፈል እንጂ የሉዓላዊነት መከበርና አለመከበር እንዳልሆነ በራሳቸው አንደበት በማያሻማ ቋንቋ ነግረውናል። በሄግ ብይን የተረጋገጠልኝ ግዛቴ ላይ አልነጋገርም የምትለው ኤርትራም የአቋም ለውጥ እያሳየች አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ፤ "ከኤርትራ ጋር የገባነው ጦርነት የሕግ የበላይነትን ለማስከበር እንጂ ለዳር ድንበር መከበር አልነበረም" የሚለው የአቶ መለስ መንግሥት አቋምም የኤርትራን አቋም የሚያጠናክር ሆኖ ይገኛል።

የኢሮብና ሌሎች የኢትዮጵያ መሬቶች ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር የመከበር ዋስትና የሚረጋገጠው የኢትዮጵያ መንግሥት በሄግ ውሳኔ መሰረት ለኤርትራ የተሰጡ የኢሮብና ሌሎች መሬቶች ሉዓላዊ የኢትዮጵያ መሬቶች እንደሆኑ በማያሻማ ቋንቋ በይፋ ሲያውጅና የአልጀርሱን ውልና የሄግ ውሳኔን ውድቅ ማድረጉን ለተባበሩት መንግሥታት ሲያስታውቅ ነው። ስለሆነም ሰራዊቱ በቦታው ተቀምጧል ብሎ መዘናጋት ሳይሆን ኢትዮጵያዊያን በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የኢሮብ ተወላጆች የኢትዮጵያ መንግስት የሄጉን ውሳኔ በይፋ መሻሩን እንዲያውጅና የኢትዮጵያ ትክክለኛው ድንበር በተባበሩት መንግሥታት በሕጋዊ መንገድ እንዲታወቅ እንዲያደረግ ሳይሰለቸን በቀጣይነት የመግፋት ግዴታችንን መወጣት አለብን እንላለን።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ወገኖች የአንድ አገር መንግሥት የሀገሩን ዳር ድንበርና ሉዓላውነት የማስከበር ግዴታ እንዳለበት ግልፅ ነውና፣ መላልሶ ማስታወስና መገፋፋት ለምን አስፈለገ? ሊሉ ይችላሉ። በመሠረቱ ለሀገር ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር መከበር ቀናዒ የሆነ መንግሥትና መሪ በሚኖርበት አገር ሲሆን አባባሉ ትክክል ይሆናል። ወደ ኢትዮጵያ መንግስትና መሪ ስንመጣ ግን ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ በትረ-ስልጣኑን ይዞ ያለው የኢህአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር በማስጠበቅ በኩል የፈጸማቸው ተግባራት ይህንን ኣያረጋግጡም። ስለዚህም ነው ዜጎች ነቅተው ለሉዓላዊነታቸውና ለዳር ድንበራቸው ዘብ መቆም አለባቸው የምንለው። በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ዳር ድንበርን ለማስከበር የቆመ መንግሥት እንዳልሆነ የመንግሥቱ ዋና ቁንጮ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ በተለያየ ጊዜ ስለ ዳር ድንበራችን ያሉትንና የወሰዱዋቸው አቋሞችን በመጥቀስ በቀላሉ ለማሳየት ይቻላል።

1) አሁን በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ ያለው ግንባር በተለይ ደግሞ የግንባሩ ቁልፍ የሆነው ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት) የኤርትራ ነፃ አወጪ ግንባሮች በ1990 ዓ. ም. በሻዕቢያ የተወረሩብን አከባቢዎችን በሚመለከት የኤርትራ "ነፃ አውጪ" ድርጅቶች፤ እነዚህ የተወረሩ አከባቢዎች የኤርትራ አካል ናቸው የሚል አቋም እንደነበራቸው ገና በረሃ እያሉም በሚገባ የሚያውቁት ጉዳይ ነው። ይህ አቋማቸው ትክክል እንዳልሆነና መስተካከል ያለበት መሆኑን ገና ከጅምሩ በሰላማዊ መንገድ ለማሳመን የህወሓት አመራር ለምን አልሞከረም? ሻዕቢያ ሰላማዊ ውይይትን አልቀበልም ብሎ ከሆነስ አከባቢውን በሃይል እንዳይወር የመከላከልያ ሃይል ለምን ገና ከጅምሩ በድንበሩ እንዲሰፍር አልተደረገም? የሚሉና መሰል ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሚሹ ናቸው።

2) ሻዕቢያ ባድሜን ወሮ ከያዘ በኋላ የተቀሩትን የትግራይና የዓፋር መሬቶች ለመውረር ዝግጅት እያደረገ መሆኑ በግልፅ እንደታወቀ የአገር መከላከልያ ኃይልን ለምን ወደ ግንባሩ አላንቀሳቀሱም? ይህን ጥያቄ ለማቅረብ የተገደድነው ሻዕቢያ ባድመን ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም. ወሮ ሲቆጣጠር፤ በኢሮብ ግንባር በኩል ወረራውን የጀመረው ግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ማለት ከ19 ቀን በኋላ መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። ሻዕቢያ የኢሮብ አከባቢን ለመውረር ዝግጅት ላይ እንደነበረ ከወረራው በፊት በሽመዛና ግንባር ሲያደርገው ከነበረው የሰራዊትና የሎጂስቲክስ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ በግልጽ ይታይ ነበር። ለምን የኢትዮጵያ መንግስት እስከ ግንቦት 23 ቀን በነበሩት ሳምንታት ውስጥ ሰራዊቱን ወደ አከባቢው ለማንቀሳቀስ አልፈለገም? ለነገሩማ ባድመ ከመያዙ በፊት ባድመን ለመያዝ ሻዕቢያ ያደርግ የነበረው ዝግጅትም ቢሆን ከኢህአዴግ የተሠወረ ጉዳይ ሊሆን አይችልም።

3) ወረራ ተካህዶ ሻዕቢያ የፈለገውን አከባቢ ሙሉ በሙሉ በቍጥጥሩ ሥር ካስገባ በኋላ በራሱ በህወሓት አመራር ውስጥ ጦርነቱን ለመመከት መወሰድ በሚገባቸው እርምጃዎችና የጦር ስልት ላይ በተደረገው ክርክር የአቋም ልዩነቶች በመከሰታቸው ከፍተኛ ውጥረት በህወሓት አመራር ውስጥ ተፈጥሮ እንደነበረ፣ የሉዓላዊነትና የዳር ድንበር ጥያቄም ለክፍፍላቸው መንስኤ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ እንደነበረ ይታወቃል። ይኸውም በነአቶ ስየ፤ አቶ ተወልደና አቶ ገብሩ የተመራውና ኋላ ከድርጅቱ የወጣው ቡድን አገር ተወራለችና ለሌሎች የግንባሩ አባል ድርጅቶችና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እናሳውቅ። ወራሪው ኃይል በወረራ ከያዘው ግዛታችን ለመውጣት ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረም ወታደራዊ ኃይላችንን ተጠቅመን ወረራውን የመቀልበስ ግዴታ አለብን ሲል፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቻቸው ግን ማንንም ሳናስታውቅ (ሸንጎውንም ጭምር) ውስጥ ለውስጥ (ህወሓት ለብቻው ከሻዕቢያ ጋር መሆኑ ነው) በመነጋገር ችግሩ መፈታት አለበት የሚል አቋም በመያዝ፤ ጉዳዩ ለተወካዮች ምክርቤት እንዳይቀርብና ወረራውን የመቀልበስ ጦርነትም እንዳይደረግ ተቃውመው እንደ ነበረ ኋላ ላይ ከድርጅቱም ከመንግሥታዊ መዋቅሮችም የተባረሩት የህወሓት መሪዎች ያዘጋጁት በነበረው ህዝባዊ የሚባል ጋዜጣ ላይ ወጥቶ አስነብበውናል። በመጨረሻ የአቶ መለስ አቋም በመሸነፉ ሳይወዱ ጉዳዩ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ወራሪው ኃይል የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶችን ለቆ ካልወጣ፣ በኃይልም ጭምር ወረራው መቀልበስ እንዳለበት በይፋ ታወጀ። ሆኖም አቶ መለስ የተጋቱት

እንጂ የወደዱት ውሳኔ ስላልነበረ፣ ኋላ ላይ አንጃ ተብለው በአቶ መለስ የተባረሩት የህወሓት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ጦርነቱን ጀምረን በአሸናፊነት ለማጠናቀቅ እንድንችል ተገቢ ዝግጅት እናድርግ ባሉ ጊዜም፤ አቶ መለስ ባለን መሣርያና ባለን የሰው ኃይል ብቻ ነው የምንዋጋው በማለት አንገራግረው እንደነበረም ተዘግቧል። አቶ መለስ ያኔ ሻዕቢያ የነበረው ኃይልና ዝግጅትን ጠንቅቀው እያወቁ ለምን ለጦርነቱ አስፈላጊውን ወጪ በማውጣት አስፈላጊ ዝግጅት በጊዜ እንዳይደረግ  መሰናከል ለመሆን እንደመረጡ ለወደፊት ታሪክ ያወጣው ይሆናል።

4) የኢትዮድያ ህዝብ አትንኩኝ ባይነትና የኢትዮድያ ሠራዊት የማጥቃት ዘመቻ የሻዕቢያን ጦር እየተከታተለ በማሽመድመድ ከሉዓላዊ ግዛቶቻችን ጠራርጎ በማስወጣት ብሔራዊ ግዳጁን ከመወጣቱ በተጨማሪ በእብሪት ተወጥሮ የነበረውን የሻዕቢያን ጥጋብ በማስተንፈስ አቅሙን እንዲያውቅ አድርጎታል። ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጦርነት የምናካሂደው ድንበርን በኃይል መለወጥ ስለማይገባ ብቻ ነው ብለውን ነበር ያረፉት። እንደ የዋኀነት ተቆጠረብን መሰል! እንደ ዜጎች መሪያቹህ ነኝ ከሚሉን ሰው ለመስማት የሚገባንን በወረራ የተያዘብን ሉዓላዊ መሬታችንን ነፃ ለማውጣት ነው የሚትለዋ ቃል አልወጣችም። በአቶ መለስ ስሌት የኢትዮጵያ ሰራዊት በወራሪው የሻዕቢያ ጦር ላይ የወሰደው የማጥቃት እርምጃ ዋና ግብ ወታደራዊ ድል ለማስመዝገብ እንጂ ሉዓላውነትን ለማስከበር እንዳልነበረ ጉልህ አድርጎ ያሳያል። በጦርነቱ ፍጻሜ ማግስት እውን የሆነውም ይኸው ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይልና በጦርነት ቀጠናው ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ለመግለፅ የሚያስቸግር መስዋዕትነት በመክፈል ነፃ ያወጧቸውን ሉዓላዊ የኢትዮጵያ መሬቶች፤ በአቶ መለስ አልጀርስ ላይ ለድርድር ቀርበው ለወራሪው ሻዕቢያ በማስረከብ የተከፈለውን መስዋእትነት መና እንዲሆን ተደርጓል። የሻዕቢያ ጦር በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ተሽመድምዶ በመፈርጠጥ ላይ በነበረበት ወቅት፤ ዳግም ለኢትዮጵያ አደጋ ሊሆን በማይችልበት ሁኔታ በማዳከም የጦርነቱ ፍጻሜ ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛቶችን በማረጋገጥ እንዳይቋጭ በማጨናገፍ፤ ጦርነቱ የኢትዮጵያን ጥቅም ሳያስከብር እንዲቆም በማድረግ፤ አቶ መለስ የተጫወቱት አሉታዊ ሚና ታሪክ የሚረሳው አይደለም። ስለሆነም በኛ በኩል ፈርተንም ሆነ በትርፍራፊ ጥቅማጥቅሞች ተደልለን ያፈጠጠውን እውነት ሸፋፍነን ለማለፍ የሚያስችል ህሊና የለንም። አቶ መለስ በጦር ሜዳ በከፍተኛ መስዋእትነት የተረጋገጠውን የኢትዮጵያ ድል አልጀርስ ወስደው በክብ ጠረጴዛ ዙርያ ለተሸናፊ ጠላት አስረክበው መመለሳቸው ማንም ሊክደው የማይችል ሀቅ ነው።

5) በወረራ የተያዘበት መሬት ከጠላት ነፃ ካወጣ በኋላ የገዛ መሬቱን መልሶ ለድርድር የሚያቀርብና ለወራሪ የሚለግስ መንግሥት ምን ዓይነት መንግሥት እንደሆነ ለመገመት የሚያስቸግር መሆኑ አልቀረም። ወደ ድርድር ከቀረበ በኋላ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ ፋንታ ለምን ወደ ገላጋይ(arbitration) ፍርድ-ቤት መሄድ እንደተመረጠ የሚያውቁት አቶ መለስና ጓደኞቻቸው ብቻ ናቸው። አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያና የኤርትራ የዳር ድንበር ጉዳይ በግልግል ፍርድ ቤት እንዲወሰን የፈለጉበት ዋና ምክንያት ሁለቱም ኤርትራን የመጥቀም ፍላጎት ስለነበራቸው እንደሆነ በፍርድ ቤት የተካሄደው የይገባኛል ሙግት፤ ባለቤትነትን ለማስረገጥ የቀረቡ ማስረጃዎችና የፍርዱ ውጤት ግልጽ አድርጎ አሳይቶናል። ጥንት የተሰረዙና የተቀበሩ ከአፄ ምኒሊክ ጋር ተደረጉ የተባሉ “ውሎችን” ቆፍረው በማውጣት ለግልግል ፍርድ-ቤት በማቅረብ ለመከራከር መወሰናቸው የሚያሳየው ይህንን ነው። አቶ መለስ በትክክል ለኢትዮድያ ሉዓላዊነት የቆሙ ሰው ቢሆኑ ኖሮ፣  አንደኛ አጼ ምኒሊክ በግድ ያኔ በነበረው ሁኔታ ተገደው (በቅኝ ገዥዎች ተፅዕኖ) የፈረሙት “ውል” መሆኑ (መቸም ያኔ መላ አፍሪካ በቅኝ ገዥዎች ተይዛ ኢትዮጵያ በጠላት ተከባ እንደነበረ የታወቀ ሐቅ ነው) እያወቁ ፤ ሁለተኛ አጼ ምኒሊክ በውሉ ማጠቃለያ ላይ ውሉ ወደ ሶስተኛ አካል (Third Party) መተላለፍ እንደማይችል በግልፅ አስቀምጠው እያለ፤ ሶስተኛ እነዛ ቅኝ ገዢዎች መላዋን ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ የነበራቸውን ህልም ለማሳካት እስክዘጋጁ ድረስ ጊዜ ለመግዛት እንዲመቻቸው የፈረሙት ‘ጊዚያዊ ውል’ በ1928 ዓ.ም. በሙሶሊኒ መሪነት ኢትዮጵያ ላይ ባደረጉት ወረራ ጊዜ ተሽሮ እያለ፤ አራተኛ ኤርትራ በተባበሩ መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ፌደራላዊ ውስጣዊ አስተዳደር ያላት የኢትዮጵያ ሉዓላዊ አካል የሆነችበት ጊዜ ተሰርዞ እያለ... ወዘተ. አቶ መለስ ከኢትዮድያ ይልቅ በግልጽ ለኤርትራ በማድላት ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ሌላውን ወገን ለመጥቀም ሲባል ብቻ ወደ ግልግል ፍርድ-ቤት መሄዳቸው ራሱ ቅንነት የጎደለው አሠራር መሆኑ ግልጽ ነው። በወቅቱ ኢትዮጵያ መምረጥ የነበረባት (መሄድ ካልቀረ) ወደ ዓለም-አቀፍ የፍትሕ ፍርድ-ቤት (International Court of Justice) ነበር። ምክኒያቱም ይህ ፍርድ-ቤት የይገባኛል ጉዳዮችን ከታሪክ ጋር በማመሳከር በጥልቀት መርምሮ የተለያዩ መመዘኛዎችንና መስፈርቶችን በመጠቀም ጉዳዩን በዝርዝር ሊመለከተውና ተገቢ ፍርድ የመስጠት ዕድል እንደነበረው ብዙ ኢትዮጵያዊያን የሕግ ባለ-ሙያዎች በወቅቱ ይጽፉ እንደነበር የሚታወስ ነው። ለምሳሌ የአከባቢው ነዋሪዎች

ወዴት ይዳኙ እንደነበረ፣ ቀረጥ ወዴት ይከፍሉ እንደነበር ወዘተ. የመሳሰሉ ነገሮችን በሚገባ መርምሮ ነው ውሳኔ የሚሰጠው። 'አርቢትረሽን' ፍርድ-ቤት ግን ሁለት ወገኖች የተስማሙበትን ነው የሚያጸድቀው። አቶ መለስ ግን ይህንን የባለሙያ ምክር ለመቀበል አልፈለጉም። ስለሆነም፤ አለመታደል ሆኖብን በኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ጉዳይ ሁለቱም ወገኖች ለአንድ ወገን (ለኤርትራ)የሚያዳሉ ሆነው ተገኝተዋል።

6) የግልግል ፍርድ ቤት ውሳኔው ይፋ በሆነበት ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ወዲያውኑ "በጦር ሜዳ ያስመዘገብነው ድል በፍርድ ቤትም ደገምነው፣ በማለት ያልጠየቅነው መሬት ሳይቀር ለኛ ተወስኖልናል" በማለት ህዝቡን ለማደናገር ሞክሯል። ይህ በሌላ ነገር ህዝብን ሸውዶ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶችን ለሻዕቢያ ለማስረከብ የተዘየደ ስልት ካልሆነ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? እንዲህ ዓይነት አቋም የሚያራምድ መንግሥት ድንበራችንንና ሉዓላውነታችንን ሊያስከብረልን ይችላል ብሎ ማመን የሚቻለው እንዴት ተብሎ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በጥንቃቄ ማብላላት ተገቢ ይሆናል።

7) ፍርድ-ቤቱ የፈረደው ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለኤርትራ መሆኑ ለሁሉም ግልፅ ከሆነ በኋላ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ፍርዱ የዓለም መንግሥታት ብይን ስለሆነ ሳንወድ በግድ መቀበል አለብን የሚል ቅስቀሳ የሚያደረጉ ካደሬዎችን ወደ ኢሮብ አከባቢ ልኮ እንደነበረ ይታወቃል። ካድሬዎቹ እንደሚመጡ ጥቆማ ደረሶት ሲጠባበቅ የቆየው የአከባቢው ህዝብም ገና እንደመጡ የቅስቀሳ ሥራቸውን ሳይጀምሩ እንዳባረራቸውም ተገንዝበናል። ካድሬዎቹ ህዝቡን ለመሰብሰብ በቻሉበት አንድ መንደር ውስጥ ከህዝብ ጋር የተካሄደውን ውይይት ውሎው እንዴት እንደነበረ እዚህ ላይ መጥቀሱ አገባብ ይሆናል። ህዝቡን ለመስበክ የተላኩት ካድሬዎች፤ በጣም እየመረረንም ቢሆን፤ ዓለም የፈረደብን ስለሆነ ውሳኔውን ሳንወድ በግድ ለመቀበል ተገደናል በማለት ድስኩራቸውን ጀመሩ። በዛ ማኸል፣ አንድ ያከባቢው አዋቂ ሰው ካድሬዎቹን  አንድ ታሪክ ልንገራችሁ አንዴ አድምጡኝ ይሏቸዋል። ካድሬዎች ለማግባብያ እንዲሆናቸው ፈቀዱና ማድመጥ ጀመሩ። ጭምቱ የአገር ሽማግሌም ለማለት የፈለጉትን እንደሚከተለው በማለት በምሳሌ አስረዱ።

"ከዕለታት አንድ ቀን ዛፎች ተሰብስበው በርካታ ወገኖቻችንን ቆርጦ ቆራርጦ የፈጀ፣ አሁንም የቀረነውንም ለመጨረስ የተዘጋጀ ወንጀለኛ ነው ብለው ፋስን ከሰው ፍርድ ቤት ያቀርባሉ። ዳኛውም የዛፎችን ክስ ከሰማ በኋላ ይህ እውነት ከሆነ ትልቅ ወንጀል ነውና ጉዳዩን መርምረን እውነት ሆኖ ከተገኘ ተገቢ ፍርድ እንፈርዳለን፤ ነገር ግን  የዚህ የፋስ ወንጀል ተባባሪ የሆነ ከናንተ ወገን እንደሌለ እርግጠኞች ናችሁን? ብሎ ዛፎችን ሲጠይቃቸው፤ ዛፎቹ መያዣውማ የኛ ወገን ነው አሉ ይባላል" በማለት ጭምቱ የአገር ሽማግሌ ንግግራቸውን እንደጨረሱ አስታወቁ። ከዛም ህዝቡ የተሸረበውን ተንኮል አስቀድሞ እንደደረሰበት የገባቸው ካድሬዎች እፍረታቸውን ተከናንበው ወደመጡበት ተመለሱ።

ሌላው በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት በዳር ድንበር ጥያቄ የማይታመን መሆኑን ለማሳየት  ራሳቸው አቶ መለስ ዜናዊ ከተናገሩት ውስጥ በመጥቀስ በቀላሉ ለማሳየት ይቻላል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከመጀመርያ ጀምሮ የሄጉን ውሳኔ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ እንደሚቀበሉ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ቃለ-መጠይቆች በተደጋጋሚ አሳውቀውናል። በቅርብ ጊዜም ሳይቀር፣ የዛሬ አንድ ዓመት፣ መጋቢት ወር ውስጥ ኣሰና ለተባለ የኤርትራውያን ሬዲዮ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ **"እኛ በፍርድቤቱ ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ቢኖረንም፤ ገና ከጅምሩ ውሳኔውን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ መቀበላችን ለተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት በጽሁፍ አሳውቀናል"** ብሏል። ለዝርዝሩ በኢሮብ ማብሎ (www.irobmablo.org) "ከኢሮብ ለኤርትራ ስለተሰጠው መሬትና የአቶ መለስ አቋም" በሚል ርእስ በመ.ኢ.ተ.ማ የወጣውን መግለጫ ይመልከቱ።

አቶ መለስ በኢትዮጵያውያን በኩል ተቃውሞ ሲበዛባቸው በ1997 ዓ.ም ኅዳር ወር ውስጥ እንዳደረጉት የድንበርን ጉዳይ በውይይት ለመፍታት ያስችላሉ በማለት በይዘታቸው ሲመዘኑ ምንም እርባና የሌላቸው ባለ አምስት ነጠብ የመደራደርያ የሚመስሉ ሓሳቦችን አቅርበው እንደነበረም የሚታወስ ነው። ሆኖም ሙከራው ከተራ አክሮባትነት የሚያልፍ ቁምነገር የለውም።  ነገሩ ያው "አልሸሹም ዞር አሉ" ዓይነት ከመሆን የዘለለ አይደለም። በዚህ መግለጫቻው ውስጥ ሰጥቶ መቀበል የሚል ነገር ቢኖርም፤ ሃቁ ግን ኢትዮጵያ የተወሰደባት እንጂ የራሷ ያልሆነ የተሰጣት መሬት የለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ እነ ፆሮናም አልጠየቅኩም የኔም አይደሉም በማለት ፍርድ ቤቱን የሞገተች መሆኑ ሲታይ፤ ለኢትዮጵያ የተሰጠ የኤርትራ መሬት ይኖራል ብሎ መገመት የሚቻል ባለመሆኑ ነው። በአካል በምናውቀው አከባቢም የተሰጠ እንጂ የመጣልን መሬት እንደሌለ እናውቃለን ። የድንበር ወሰን ሲሰመር አንድ ቤት ለሁለት እንዳይከፈል የሚባለው ዓይነቱ ቋንቋም ተራ የቃላት ጨዋታ እንጂ ወሰን ሲሰመር አንድ ህንፃን ለሁለት አለመሰንጠቅ የታወቀ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ እንኳን አንድ ቤት አንድ ሶስተኛ የኢሮብ ለም መሬትም እየተሰጠ ስለሆነ የአንድ ቤት ለሁለት መከፈል የሁለት መንግሥታት ውይይትና ስምምነት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። ያም ሆነ ይህ ከሰሜን ኢትዮጵያ፣ በተለይ ከኢሮብ፣ ለኤርትራ የተለገሱ መሬቶች የብዙ

ዓሠርት ኪሎመትሮች ርዝመትና ስፋት ያላቸው እንጂ በአንድ ቤት ወይም በአንድ መንደር የሚወሰኑ አይደሉም። ለዝርርዝሩ " No one is entitled to infringe on the unity of the Irob people" በሚል ርእስ በመ.ኢ.ተ.ማ. የተሰራጨውና በተለያዩ ድረ-ገጾች የተለጠፈውን መግለጫ ይመልከቱ።

በአሥመራ ስልጣን ላይ ያሉት አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ አልነጋገርም ማለታቸው በጀ እንጂ፤ ዛሬ እነዛ የኢትዮጵያ ሠራዊት አለበትና "አያሳስብም" የሚባሉ አከባቢዎች እንደ አቶ መለስ አባባል ከሆነ በሰጥቶ መቀበል ስልት አልቆላቸው በኤርትራ ባለቤትነት ሥር ገብተው ሊገኙ ይችሉ ነበር። አቶ መለስ ዜናዊ ከላይ ለተጠቀሰው አሰና ሬዲዮ ጣቢያ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ላይ ለኤርትራ ተሰጠ የተባለው አከባቢ ቁጥር ውስጥ የሚገባ ስፋት ያለው መሬት አለመሆኑን ሲያስረዱ እንደሚከተለው ብለው ነበር፡ **"ኤርትራን እንዳለ ሰጥተን አሁን አንድ ሁለት ወይም ሶስት መንደሮች ወደኛ መምጣት ለኛ ምንም አያደርግልንም። በኮምሽኑ ውሳኔ መሰረት ድንበሩን ለማካለል በኛ በኩል ዝግጁ ነን። እኛ እያልን ያለነው የድንበሩን መስመር በመሬቱ ላይ ለማስመር እንነጋገር ነው።"** ይህ ብቻ አይደለም ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ለአከባቢው ህዝብ ተቃውሞም ዋጋ እንደማይሰጡና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በኃይል ከመጨፍለቅ የሚያግዳቸው ነገር እንደማይኖር በቃለ-መጠይቁ ላይ እንዲህ በማለት ጠቆም አድርገውናል፡ **"የድንበር መስመር አከላለልና አፈጻጸሙ ላይ ለመነጋገርም ሻዕቢያ ዝግጁ ከሆነ አንዳንድ ማንገራገሮች በአንዳንድ አከባቢ በህዝቦች መከሰቱ እንኳ የማይቀር ቢሆንም፤ ይህን ሁሉ ተቋቁመን በኛ በኩል ለመነጋገሩም ሆነ ድንበሩን በኮሚሽኑ ውሳኔ መሰረት ለማስፈጸም ዝግጁ ነን" ብለዋል**። ይህን የሚል መሪ የያዝን መሆናችን ስለምናውቅ ነው እኛው ራሳችን ለሉዓላዊነታችንና ለዳር ድንበራችን ዘብ እንቁም የምንለው።

ዛሬ በኢትዮድያ በትረ ስልጣኑን ይዞ ያለው በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት በዳር ድንበር ጥያቄ ላይ ያለው አቋም ከላይ የተገለጸውን ይመስላል። ይህ ዓይነት መንግስት ይዘን ዳር ድንበራችን ይከበርልናል ብለን ለመረጋጋትና ለመዝናናት የሚያስችለን መተማመኛ የለም። በመሆኑም ያለን አማራጭ ሁለት ብቻ ነው። "እግሬን ነው እየበላ ያለውና እንዳይሰማን ዝም በል" ዓይነት ዝምታን መርጠን ቁጭ ማለት አልያም ለዳር ድንበራችን ሰበብ ሳናበዛ አንድ ላይ መታገል።

በርግጥ የኢሮብ ህዝብም ሆነ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ አንደተለመደው ለዳር ድንበሩ ይዋደቃል እንጂ ስንዝር መሬትም ብትሆን ከዳር-ድንበሩ ቆርሶ እንደማይሰጥ ሙሉ እምነት አለን። ነገር ግን ሌላ ችግሩ እንዳይበቃው ለምንድነው ህዝባችን በዚሁ ባልተረጋጋ የድንበር ጉዳይ እየተጨነቀ የሚኖረው? የሚለው ጥያቄ ለጊዜውም ቢሆን ያሳስበናል። ምክንያቱም ያልተረጋጋ የድንበር ሁናቴ እስካለ ድረስ ህዝባችን የረጂም ጊዜ እቅድ አውጥቶ እየሠራ ተዝናንቶ መኖር አንደማይችል የታወቀ ስለሆነ ነው። አከባቢያችን በድርቅ፣ በሥራ እጦት፣ በበሽታ ወረርሽኝ ወዘተ. የተወጠረ አከባቢ ነውና ቢያንስ ስለ ድንበር መጨነቅ ከጀርባው መውረድ አለበት እንላለን። ይህንን ማድረግ ያለበት ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው። በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮድያ መንግስት እስከዛሬ በሀገር ሉዓላዊነትና በዳር ድንበር ጥያቄ ላይ ያራመደው አቋም የተሳሳተ ነው። ስለዚህም ነው እኛው ዜጎች ለዳር ድንበራችን ራሳችን ዘብ እንቁም፣ በመንግስቱ ላይም ማሳደር ያለብንን ተጽዕኖ ለማሳደር ባንድነት እንረባረብ የምንለው።

<u>ማጠቃለያ</u>

በኢትዮጵያና ኤርትራ ድንበር በሄግ ውሳኔ መሠረት የተባበሩ መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ኃይል ሰፍሮ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ሆኖም ሻዕቢያና የሻዕቢያን ሠራዊት ለሄግ ውሳኔ ተገዥ እንዲሆኑ ለማድረግ አልተቻለውም። ስለሆነም፤ ኤርትራ የአልጀርስና የሄግን ውሳኔዎች ሙሉ ለሙሉ ጥሳለች። በመሆኑም፡ ኤርትራ ራሷ የጣሰችውን የአልጀርስን ውል ኢትዮጵያ ተሸክማው እንድትኖር የምትገደድበት ምንም ምክንያት ስለሌለ ስምምነቱን ውድቅ ማድረግ ይኖርባታል። እስካሁን ግን አላደረገችውም። ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ መንግሥት ለኤርትራ ስለ ተሰጡ የኢትየጵያ ሉዓላዊ መሬቶች እንደማይጨነቅ ነው። ስለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን ባጠቃላይ በተለይ ደግሞ በቀጥታ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁኔታውን ነቅተው በመከታተል ለአገራችን ሉዓላውነትና ለድንበራችን መከበር ዋልታና መከታ ሆነው መቆም ይኖርባቸዋል የምንለው። ለሉዓላዊነትና ለዳር ድንበር መከበር የሚደረገው ትግል ደግሞ ምንም ዓይነት የፖለቲካም ሆነ የርእዮተ-ዓለም ልዩነት ሳይገባበት፣ አሁን ስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የሚደግፉም ሆነ የሚቃወሙ ሁሉ በትብብር ማድረግ ያለባቸው ግዴታ ነው። የድንበር ጥያቄ በተወሰነ ጊዜ በስልጣን ላይ የሚኖረው መንግሥት መደገፍና አለመደገፍ ጋር መያያዝ ያለበት ጉዳይ አይደለም ። የአገር ዳር ድንበርን ለማስከበር በሚደረገው ትግል የዳር ተመልካች ሆኖ ቁጭ ማለት ኣይገባም። የታሪካችን ተመክሮ የሚያሳየው ኢሮቦችም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በዚህ መስክ የታወቁ መሆናቸውን ነው። በአልጀርስና በሄግ ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመ ወንጀልን በሚመለከት የኢትዮጵያ ምሁራንና የኢሮብ ተወላጆች የጥናትና የተቃውሞ ጽሑፎች የሚያመለክቱትም ይህንኑን ነው።

በመሆኑም ለታሪክ ተመራማሪዎች የምርምር መነሻ እንዲሆን፤ አሁን ላለነው ዳር ድንበርን የማስከበር ትግላችንን አጠናክረን እንድንቀጥል እንደ አቅጣጫ አመልካች እንድንጠቀምበትና መጪው ትውልድም በወቅቱ ያለውና የነበረውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል በጭብጥ የተደገፈ መረጃ ለማግኘት ይቻላቸው ዘንድ በማሰብ፤ ለደጉም ለመጥፎም ታሪክ እንዳለ መዘገብ አለበት ከሚል እምነት በመነሳት www.irobmablo.org ድረ-ገጽ የኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ግጭትን በሚመለከት የተጻፉ አገባብነት አላቸው ብሎ ያመነባቸውን ሰነዶች የሚያሰፍርበት አዲስ አምድ ይኖረዋል። እስከዛ ድረስ ድንበርን በተመለከተ ያሉዋችሁ የቆዩም ሆነ አዳዲስ መጣጥፎችን እንድትልኩልን በትህትና እናሳስባለን።